የካቲት 12 ቀን 2015 ዓ/ም



እጅግ ለማከብረዎ አባቴ ቆሞስ አባ ሠረቀብርሃን ወልደ ሣሙኤል፡፡

ባለፈው ሳምንት ስደውልለዎ “ዘይፌውስ ቁስለ ሥጋነ ወመንፈስነ ወነፍስነ” እያልን በመማጽን የምናመልከው አምላክ በሰጠኝ ድፍረት ነው፡፡

ላጭር ጊዜ በስልክ በተገናኘን ጊዜ  ከድምጻወ የወጣችውን ሰላምታ ስሰማ እጅግ በጣም ደስ አለኝ፡፡ መልሰው እንደሚደውሉልኝ ስለነገሩኝ በተስፋ ጠብቄ ነበር፡፡ አልተመቼወም መሰለኝ አልደወሉልኝም፡፡

በአማራው ምድር ከተወልዱ መንፈሳውያን ሰወች ከኔ በፊት ደውለው ሰላም ያሉወት ካሉ በመዘግየቴ፤ የመጀመሪያው ከሆንኩም በመድፈሬ ይቅርታ እጠይቃለሁ፡፡

በወገን ላይ የደረሰውና የሚደርሰው አሰቃቂ መከራ በንብ እሾህ ለሚቆጣው ሰውነታችን እጅግ ይከብዳል፡፡ ቁጣ የባህርያችን ስለሆነ ሁላችንም ተቆጥተናል፡፡ ተገቢም ነው፡፡ መቆጣትን ማልቀስን መሳቅን አምላካችን ለጥቅማችን የባህርያችን እንዲሆን ሰርቶልናል፡፡

ቁጣ ጠቃሚ ባይሆን ኖሮ ቅዱስ ጳውሎስ “ተቆጡ” ባላለም ነበር፡፡  ቁጣ ቋሚ መመሪያ እንዳይሆነንም

"በቁጣችሁ ላይ ጸሐይ አይግባ" አለ፡፡ ሕሊናችን ቁጣ ጸንሶ ከዋለና ካደረ ከቁጥጥር ውጭ በማድረግ ስህተት ስለሚያሰራ "ለዲያብሎስ ፈንታ አትስጡት (ኤፌ 4፡26) አለ፡፡ ቁጣ ከእግዚአብሔር ፈቃድ ስለሚያርቅ ቅዱስ ያዕቆብም "መአቱ ለብእሲ ኢያጌብሮ ጽድቀ እግዚአብሄር"(ያዕ) ብሎ ነግሮናል፡፡

ይሁን እንጅ በወገኖቻችን ላይ የተፈጸመው አሰቃቂ በደል መቆጣት ብቻ ሳይሆን "አኮ ባሕቲቶ ቃለ እግዚአብሔር ወዓዲ ነሰነሂ" እንዳለው ብንታደል ኖሮ በሩቅ ሆነን ድምጽ ማሰማት ብቻ ሳይሆን በሚጋደሉትና በሚገደሉት መካከል ገብተን በመገላገል ሞቱንም የመካፈል ግዴታ ነበረብን፡፡

ይህ ከባድ እዳና ሐላፊነት እያለብን ዝም ማለት "ወዘሰ ኢይሄሉ ለቤቱ ወይገድፍ አዝማዲሁ ውእቱ ክህደ ሃይማኖቶ ወየአኪ እምዘኢየአምን" (1ኛ ጢሞ 5፡8)፡፡ እንዳለው ሃይማኖት ከሌለው ካረመኔ የከፋ ነው፡፡ ሁላችንም እስካሁን ተናገርን ጮህን አለቀስን አሁንም ህዝባችን እየሞተ ነውና ጩኸታችን ይቀጥላል፡፡

ሆኖም "ኃዘን ኢይባእከ እስመ ብዙኅን እለ ሞቱ እንበይነ ኃዘን እስመ ኃዘኑ ለልብ ይሰብሮ ለኃይል፡፡ ወአእምር ከመ አልባቲ ፈውስ ወር እሰከኒ ታሐ ወአርልቦ ዘትበቁዕ"(ሲራ38፡ 16_21) እንዳለው በመጠንና በተገቢ ካልሆነ ለቀሪው ሕዝባችንና ለራሳችን ምንም እንደማይጠቅም ይመክረናል፡፡ በሰውነታችን ተቀናጅተው ህልዋን የሆኑ ከቁጣ

ጋራ ሌሎችም ለሞተና ለተጎዳ ወገን እንድናዝን እንድናለቅስ የተፈጥሮ ግዳጅና በውስጣችን ያሉ ናቸው፡፡



አካል ሲቃጠል የጣታችን ነርቭ የጠቅላላ ሰውነታችንን ውሳኔ ሳትጠብቅ በተቃጠለበት አካል ለማረፍ ቅጽበት እንደማትቀድማት፡ በወገን ላይ ለሚደርሰው ወገን ለማልቀስ የጎረቤት ምክርና ሐሳብ አይጠበቅም፡፡ በዚህም ሁኔታ ሁላችንም ሳንማከር በቀረቡን ወገኖቻችን ላይ ለደረሰው መከራና ስቃይ በየግላችን አልቅሰናል፡፡የሀዘንና የቁጣ ድምጻችንንም አሰምተናል፡፡

የዚህ ሁሉ መነሻወችም ሲራክ "ሀለወ ዘይጠበብ ወይጠናቀቅ እንዘ ይ ዔምጽ ወንዘ ይመይጣ ለምክር ወያስተርኢ ከመ ያድሉ ለቢጹ ወከ ያስተራትዕ ፍትሐ ለማኅፈሩ"(19፡22) እንዳለው፡ ከራሳቸው ስሜትና ፈቃድ ራቅ ብለው የማያዩ በእጅ በሚዳሰሱት በዓይን በሚታዩት ነገሮች ላይ የሚያተኩሩ ፖለቲከኞች ወገኖቻችን በፈጠሩት የመገዳደልና የማጋደል ተግባራቸው ነው፡፡

እኛ መንፈሳውያን ሰወች ግን "ምናሴ ይበልኦ ለኤፍሬም ወኤፍሬም ይበልኦ ለምናሴ. . . . ወዐዲ ቁጣሁ ለእግዚአብሔር ኢተመይጠት "(ኢሳ 9፡19_22) ፡፡ ከሚለው በመማር የሕዝባችን የእርስ በርስ መጋደል አዲስ ሊሆንብን የሚገባ አይመስለኝም፡፡

መጽሐፋችን “መንግሥትሰ ትትፋለስ እምሕዝብ ለሕዝብ እንበይነ አምጻ ወእንበይነ ጋእዝ ወነዋይ” 10፡8 እንዳለው፡፡ መንግሥት በግድያ በውዝግብ በሸንገላ ካንድ ወገን ወደ ሌላ ወገን ሲሻገር በግድያና በዘርፊያ እንደሚሆን ተምረናል፡፡



“ከመ  ቆጽለ ዕጽ ዘጽፋቅ ቆጽሉ ዘቀዳሚ ይትነገፍ ወዘደገሪ ይሰርጽ ከማሁ  ኩሉ ትውልድ ዘሥጋ ወደም ዝከቱ ይትወለድ ወዝከቱ ይመውት” (14፡18) እንዳለው የሕብረተ ሰብ ትውልድም በሰው ሰራሽና በተፈጥሮ ያልፋል፡፡ ይተካል፡፡ በሚተካው ትውልድ የቂምና የበቀል ውርስ ላለማሻገር ከሥጋውያን መሪወች ይልቅ በኛ ላይ ድርብ ኀላፊነት አለብን፡

የቀኖናችን መጽሐፍ “ሀሉ አንተ እንበለ ሐሜት ከመ ኢይትዐቀፍ በእንአቲከ አሀዱሂ እምሕዝባዊ  ያስተሐምም በነፍሱ፡፡ አንተሰ ጾርከ ክቡደ ጾረ”(ፍ አ 5፡ 120) እንዳለው ዓለማውያን ፖለቲከኞች ዓለምን የሚተረጉሟት ከዓለም ባገኙት መነጸር ነው፡፡ እኛ መንፈሳውያን መሪወች ግን ከፖለቲከኞች (ዓለማውያን) የበለጠ እዳ አለብን፡፡

“ይትረኀዋ አእዛነ ልብ ዘውስጥ ይትከሠታ አዕይንተ ልብ ዘውስጥ ወአኮ ዘአፋአ”(ቅ አ ቁ 14) እያልን አምላካችንን የምንማጸን በመሆናችን የሚመጣውን መከራ ከፖለቲከኞች አስቀድመን አይተን ፖለቲከኞች ወገኖቻችንን ከቁጣ ከንዴት ከበቀልና ከእልክ ወጥተው ለትውልድ የሚጠቅመውን እንዲሰሩ የመጠቆምም ሐላፊነት አልብን፡፡

ወገኖቻችን ፖለቲከኞች ለትውልድ የሚጠቅመውን እንዲሰሩ እኛም በሐሳብ ማገዝ የምንችለው "እግዚእ እግዚእ እግዚአብሔር አብ አኃዜ ኩሉ ዓለም አንተ ውእቱ ዘትርፌውስ ቁስለ ነፍስነ ወሥጋነ ውመንፈስነ"(ቅ ሐ ቁ 79) እያልን የምንማጸነው አምላክ የደረሰብንን የሥጋ የመንፈስና የነፋስችንን ቁስል ሲፈውስልን ብቻ እንደሆነ የሁላችንም እምነት ይመስለኛል፡፡

ካባቶቻችን ሊቃውንት አንዱ እንደኛ ከህዝባቸው ርቀው በነበሩበት ወቅት በህዝባቸው ላይ የደረሰውን መከራና ሥቃይ ሰምተው የተሰማቸውን ሀዝንና ትካዜ በገለጹበትን ቅኔ እሰናበተወታለሁ፡፡

"ኢይጻእ ሰብእ እምአንቀጸ ቤቱ፡-እስመ አረጋዊ ዘወጽአ እምአንቀጸ ገነት ንድቅ፤

መተረ ቆጽለ ተስፋ ኪሩቤል አዕጹቅ

በእደዊሃ ለሄዋን ደቂቅ፡-

ወዘወጻእ እማሕደሩ፤ መድኃኔ ዓለም ፈደየ ዕዳሞተሰብ ወርቅ፡

አነኒ ድሕረ ወጻእኩ እምህገርየ ርኁቅ፡

በዝ ብሔረ ባእድ ተንተንኩ ለወዲቅ፡

ወጻሐየ ደዌ ሠረቀ እምልቡናየ ምሥራቅ፡

ለሰብእ መከራሁ አኮኑ ኢየሀልቅ"

በአገርም በውጭም የክርስቶስን መከራና ትንሳኤ እያሰብን ይህንን ጾም  በደስታም ጊዜ በያመቱ እንጾመዋለን፡፡ በያመቱ ስንጾመው የክርስቶስን ስቃይ ዓመታዊውን እሳቤን ለማድረስ ብቻ አይደለም፡፡ "እኔ የስራሁትን ትሰራላችሁ ከዚያም የበለጠ ትሰራላችሁ" (ዮሐን 14፡ )እንዳለው ያለንበትን የጨለማ ዘመን የመሰለ ክፉና ፈታኝ ዘመን ሲገጥመን ያልታየ እንድናይበት የተሰወረ የምንገልጥበት የፈረሰ የምንገነባበት የተሰበረ የምንጠግንበትን አዕምሮ ጉልበትና ኃይል ለማግኘት ነው፡፡

በተረፈ ""እግዚእ እግዚኦ እግዚአብሔር አብ አኃዜ ኩሉ ዓለም አንተ ውእቱ ዘትርፌውስ ቁስለ ነፍሰነ ወሥጋነ ውመንፈስነ"(ቅ ሐ ቁ  እያልን የምንማጸነው አምላክ ከደረሰብን ቁስለሥጋ፤ ቁስለነፍስና  ቁስለመንፈስ ፈውሶ የይቅርታ የሰላም የመዋዳድ የመተዛዘንና የመስማማት መንፈስ ይዘን በሕዝባችን መካከል ብቅ በማለት የዘንድሮውን ትንሳኤ ለማክበር ያብቃን፡፡

"ኦ አቡየ ተዘከረኒ በጸሎትከ ቅድስት"